ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረቢዕ አውል 16/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር አክቶብር 22/2021 ግ.

(1)

## የነብዩ (ሶ.ዐ.ወ.) አስተማሪና አሳዳጊነታቸው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ اللَّهِ لِنتَ لَهُمْ}

ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብከላቸው፡፡ ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለታላቁ አላህ ይገባው፡፡

ብቸኛ አጋር የሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ እንድሁም ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸው እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በማሳደግ ዘዴያቸው የበላይነት እንድሁም በማስተማር ቅንነታቸው ለሰው ልጅ ሁሉ ታላቅ አርአያ ነበሩ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ርህሩህ አስተማሪና ጥበበኛ አሳዳጊ ነበሩ፡፡ በእዝነት የሚመሩና በውብ ዘዴ የሚያስተመሩ አርኣያም ነበሩ፡፡ እሳቸውም እንደዚህ ይሉ ነበር፡ (አላህ ከአቀም በላይ ባለ ነገር አስገዳጅ ወይም ግትር አድርጎ ወደሰዎች አላከኝም፡፡ ነገር አስተማሪና ነገሮች ልዝብ አድራጊ ስሆን ነው የላከኝ)፡፡ እንዲሁም እንደዚህ ይሉ ነበር፡ (ርህሩህነት በአንድ ጉዳይ ላይ

አይገኝም የሚያውበው ቢሆን እንጂ፡፡ ከአንድ ጉዳይም አይሰወርም ነውረኛ የሚያደርገው ቢሆን እንጂ)፡፡

የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.)የሕይወት ታሪክ የሚመራመር ሰው (ከነርሱ አላህ ይውደድና) የባልደረቦቻቻው ብሎም የመላው የሰው ልጅ ደግ አስተማሪ መሆናቸወን እንዲሁም አሳቸውም (ሶ.ዐ.ወ.) ለፍጥረታት ከማነም የበለጡ አዛኝ፣ ሲያስተምሩ ሲያሳድጉና ቅኑን መንገድ ሲመሩም አሁንም ከማነም የበለጠ ርህሩህ መሆናቸውን ይገነዘባል፡፡

እነሆ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዊያ ቢን አልሐከም እንዲህ ይላሉ፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን እኔ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር እየሰገድኩ ሳለ ከሰዎቹ አንዱን አነጠሰው፡፡ እኔም አላህ ይማርህ አልኩኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ሰዎች በአይናቸው ገለማጡኝ፡፡ እኔም ወይኔ ጉዴ ምነካችሁ ለምን እንደዚህ ትመለከቱኛላችሁ አልሁኝ፡፡ እነሱም በእጆቻቸው ጭኖቻቸውን ይመቱ ጀመር፡፡ ዝም ሊያሰኙኝ እየሞከሩ መሆኑን ተገነዘብሁና ዝም አልኩኝ፡፡ የአላህ መለክትኛ ስግደታቸውን ከጨረሱ በኋላ በእናቴና በአባቴ የምዋጃቸው ስሆን ከሳቸው በፊትም ከሳቸው በኋላም አንደሳቸው ደግ አስተማሪ አይቼ አላውቅም፡፡ በአላህ ይሁንብኝ አልተቆጡኝም አልመቱኝም አልሰደቡኝምም፡፡ ብቻ እንደዚህ አሉኝ፡ (እነዚህ ስግደቶቻችን በነሱ ውስጥ የሰዎች ንግግር አይፈቀድባቸውም፡፡ ነገር ግን የፈጣሪ ውዳሴ አክብሮት አምልኮትና የቅዱስ ቁርኣን ንባብ ብቻ ይፈቃዳሉ)፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ኡማማ እንዲህ ይላሉ፡ «አንድ ወጣት ወደ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጣና ያላህ መልክተኛ ሆይ ዝሙትን ይፍቀዱልኝ አለ፡፡ በዚይን ጊዜ ሰዎች ወደሱ ዞሩና ገሰጹት፡፡ ኧረ ዝም በል ዝም በል አሉት፡፡ ነብየችን ግን እስኪ ና ወደኔ ጠጋ በል አሉት፡፡

(3)

እሱም ተጠጋ ከዚይም ተቀመጠ፡፡ ነብያችንም እነዲህ አሉት (ይህ ጽያፍ ነገር በናትህ ላይ ቢፈጽም ደስ ይለሃል ? አሉት፡፡ እሱም በአላህ ይሁንብኝ ያለህ መልክተኛ ሆይ አላህ ለርሰዎ ዋጅ ያድርገኝና ጭራሽ ደስ አይለኝም አለ፡፡ እሳቸውም ሰዎችም ሁሉ በናቶቻቸው ላይ ይህ ጽያፍ እንዲፈጸም አይወዱም አሉት፡፡ እንገናም በሴት ልጀህ ላይ እንዲፈጸም ተፈቅዳለህን አሉት፡፡ እሱም በአላህ ይሁንብኝ ያለህ መልክተኛ ሆይ አላህ ለርሰዎ ዋጅ ያድርገኝና አልፈቅድም አለ፡፡ እሳቸውም እንደዚሁ ሰዎች ሁሉ በሴት ልጆቻቸው ላይ እንዲፈጸም አይፈቅዱም አሉት፡፡ አንደገናም በአህትህ ላይ እንዲፈጸም ተፈቅዳለህን አሉት፡፡ እሱም በአላህ ይሁንብኝ ያላህ መልክተኛ ሆይ አላህ ለረሰዎ ዋጅ ያድርገኝና አልፈቅድም አለ፡፡ አሳቸውም አንደዚሁ ሰዎች ሁሉ በእህቶቻቻው እንዲፈጸም አይፈቅዱም አሉት፡፡ አሁንም በአክስትህ ላይ እንዲፈጸም ትፈቅዳለህን አሉት፡፡ እሱም በአላህ ይሁንብኝ ያላህ መልክተኛ ሆይ አላህ ለርሰዎ ዋጅ ያድርገኝና አልፈቀደውም አለ፡፡ እሳቸውም እንደዚሁ ሰዎች ሁሉ ለአክስቶቻቸው አይፈቅዱትም አሉትና እጃቸውን ከላዩ ላይ ጣል አድርገው እንዲህ አሉ፡( ጌታዬ ሆይ ለወንጀሉ ምህረት አድርግለት፡፡ ልቡንም አጽዳለት፡፡ ሀፍረተ ገላውንም ጠብቅለት)፡፡ ያ ወጣት ከዚያ በኋላ ወደምንም ነገር ዞር አይልም ነበር፡፡»

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የነብያችንን ((ሶ.ዐ.ወ.) የሕይወት ታሪክ ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው የሰበካና የትምህርት ዘይቢያቸውን የተለያየ ለማድረግ ጥረት ያደርጉና ወደ ተደራሹ አእምሮና ልቦና ለመድረስ በርካታ የሰበካ መገናኛ ክህሎቶችን ይጠቀሙ አንደበር፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ለመረዳት እንዲቀል የአኃዝ ቋንቋን ይጠቀሙ እንደበር ሊገነዘብ ይችላል፡፡

ለምሳሌ እንደዚህ ይላሉ፡ (ሦስት ነገሮች በልቦናው ያደሩ ሰው የእምነትን ጣእም ያገኛል፡፡ (እነሱም) አላህን መልክተኛው ከነሱ ሌላ ካለ ነገር ሁሉ ይበልጥ በልቡ ዘንድ የተወደዱ መሆናቸው፡፡ አንድን ሰው ሲወድ ለአላህ ብሎ እነጂ ለሌላ ነገር የማይወደው መሆን፡፡ አላህ ከሱ ካዳነው በኋላ አንደገና ወደክህደት መመለሰን ወደእሳት መወርወርን እንዲሚጠላ ዓይነት አድርጎ መጥላት) ናቸው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንዳንድ ጊዜ የማብራሪያ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያስተምሩ ነበር፡፡ ለምሳሌ እንደዚህ ይሉ ነበር፡ (የደግ አቀማማጭና የመጥፎ አቀማማጭ ምሳሌ እንደ ምስክ ተሸካሚና እንደወናፍ ነፊ ነው፡፡ ምስክ ተሸካሚ፡ ምስክ ይሰጥሃል ወይም ከሱ ምሰክ ትገዛለህ፡፡ አለዚይም በመልካም ጠረኑ ያውድሃል፡፡ ወናፍ ነፊ ደግሞ ልብስህን ያቃጥላል አለዚያም መጥፎ ሽታው ያስቸግርሃል)፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሌላ ጊዜ ደግሞ ተደራሹን ለመሳብ፣ በቀላሉ ለማስተማርና ንቃተ ህሌና ለመስጠት ጥያቄ የመሰንዘር ዘዴን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ለምሳሌ እንደዚህ ይላሉ፡ (ድሃ ማለት ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን ሰዎችም ድሃ ማለት ገንዘብና ንብረት የሌለው ሰው ነው በማለት መለሱ፡፡ ነብያችንም (ሰ.አወ.) እንዲህ አሉ፡ ከኔ ህዝቦች ድሃው በቂያማ ቀን ስግደቶች፣ ጾሞችና ምጽዋቶች ይዞ ምጥቶ በሌላም በኩል

ይህን ሰድቦ፣ ያን ዘልፎ፣ የዚህን ገንዘብ በልቶ ያዚያን ደም አፍሶና ይህን መትቶ በመምጣቱ ይህ ከመልካም ሥራው ይሰጣል፡፡ ያም ከመልካም ሥራው ይወስዳል፡፡ ያለበትን ሁሉ ሳይከፍል መልካም ሥራው ያለቀ ከሆነ ከነሱ ኃጢያት ተወስዶ ከሱ ላይ ይጣላል፡፡ በዚህ ምክንት ወደ ገሀንም ይጣላል፡፡ ይህ ነው ድሃ ማለት)፡፡

እንደዚሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለማስተማርና ቅኑን መንገድ ለመምራት ተስማሚ ቀናትና ጊዚያትን ይመርጡ ነበር፡ «ከርሳቸው አላህ ይውደድና አብደላህ ኢብን መስዑድ እንዲህ ይላሉ፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዳንሰለች በፍራት በተወሰኑ ቀናት ምክርና ተግሳጽ ይሰጡን ነበር»

እኛ በአሁኑ ወቅት የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) መልእክት ለማሰራጨትና ቅን መንገዳቸውንና ፈለጋቸውን ለማብራራት በምናስተምርበትም ሆነ በምንማርበት ወቅት የሳቸውን ጠባይ አርኣያ ማድረግ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡

ጌታዬ ሆይ! ትምህርትንና መልካም ስርኣትን ለግሰን፡፡ የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ጠባይ እንዲንጎናጸፍም ቅኑን መንገድ ምራን፡፡